የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷፬
አዲስ አበባ ነሃሴ ፳፩ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 64
ADDIS ABABA 27th August 2013

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፺፬/፪ሺ፭ ዓ.ም.
የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ…………………………… ገፅ ፯ሺ፸፬

## CONTENTS

Regulation No. 294/2013
Tourism Transformation Council and Ethiopian Tourism Organization Establishment Council of Ministers Regulation ………………….. Page 7074

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፬/፪ሺ፭

## የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፬-/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ቱሪስት" ማለት በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢ ለጉብኝት፣ ለመዝናናት፣ ዘመድ ወይም ወዳጅ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ዓለምአቀፍ ጉባዔዎችን ለመሳተፍ፣ ለጥናትና ምርምር፣ ሀይማኖታዊ ግዴታዎችን ለመወጣት፣ የስፖርት ዝግጅቶችን ለመከታተል ወይም ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ አገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሰበት ቦታ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ሰው ነው፤

፪/ "ቱሪዝም" ማለት ቱሪስቶች በሚያደርጉት ጉዞ፣ ጉብኝትና ቆይታ በሚያካሂዱት እንቅስቃሴና ግንኙነት የሚፈጠር ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ክስተት ነው፤

፫/ "የቱሪዝም ልማት" ማለት በማንኛውም የአገሪቱ ክልል የሚገኙ ባህላዊ እሴቶችን፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን፣ ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን በዘላቂነት በማልማት እንዲጠበቁና ለህዝቦች ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ለማድረግ የሚከናወን ሥራ ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 294/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE TOURISM TRANSFORMATION COUNCIL AND THE ETHIOPIAN TOURISM ORGANIZATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 35 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended).

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Tourism Transformation Council and Ethiopian Tourism Organization Establishment Council of Ministers Regulation No. 294/2013".

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "tourist" means a person who travels into any part of the country from his regular home for vacation, recreation, visiting relatives or friends, meeting, conference, study and research, accomplishing religious obligations, attending sport events or for any other purpose and stays at a destination for no more than one year;

2/ "tourism" means economic and social occurrences that result from interactions of travel, tour and stay activities of tourists;

3/ "tourism development" means sustainable development and conservation activities in an attempt to promote economic and social significances of cultural values, historic and natural assets and building up new and enhancement of existing tourist destinations found in any part of the country;

፬/ "የቱሪዝም ማርኬቲንግ" ማለት የዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ጐብኝዎችን ፍላጐት በማጥናት የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ የቱሪስት መዳረሻዎች፣ የቱሪዝም ምርቶችና አገልግሎቶች የሚመለከቱ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን፣ የቱሪስት ፋሲሊቴሽን ሥራዎችን በማከናወን የቱሪዝም ሀብቶችን በስፋት በማስተዋወቅና የሽያጭ ተግባራትን በማካሄድ አገሪቱ ከቱሪዝም ዘርፍ የምታገኘውን ጠቀሜታ ለማሳደግ የሚከናወን ሥራ ነው፤

፭/ "የቱሪዝም ተዋናይ" ማለት በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ አካላትን፣ መንግስትን፣ የግል ባለሀብቱን፣ ማኅበረሰቡንና ቱሪስቱንም ጭምር የሚያጠቃልል ነው፤

፮/ "የቱሪስት መረጃ ማዕከል" ማለት ቱሪስቶች አገሪቱን ለመጎብኘትና በአገሪቱ ለሚኖራቸው ቆይታ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የሚደራጁበትና በአካል፣ በስልክ ፣ በፋክስ፣ በኢ-ሜይል እና በመሳሰሉት መንገዶች መረጃ የሚሰጥበት ተቋም ነው፤

፯/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፰/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት
## የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት

### ፫. መቋቋም

የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

### ፬. የምክር ቤቱ አባላት

፩/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ............ ሰብሳቢ፤

ለ) ሚኒስትሩ.................... ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ) የቱሪዝም ቦርድ ሰብሳቢ ................. አባል፤

4/ "tourism marketing" means enhancement of the country's tourism benefits by way of organizing and analyzing data pertinent to tourist attractions, tourist destinations, tourist products and services on the basis of study of international and domestic tourists' expectations, and by way of tourist facilitation activities and extensive promotion and sales of tourism resources;

5/ "tourism actors" means players of the tourism sector including government bodies, the private sector, the community and the tourist;

6/ "tourist information centre" means an establishment that organizes information vital to tourists to travel into the country and entice them to stay longer and provides directly to its visiting enquirers virtually and through telephone, fax, e-mail and other similar ways;

7/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Culture and Tourism, respectively;

8/ "region" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## TOURISM TRANSFORMATION COUNCIL

### 3. Establishment

The Tourism Transformation Council (hereinafte "the Council") is hereby established.

### 4. Members of the Council

1/ The Council shall have the following members:

a) the Prime Minister ................ Chairperson;

b) the Minister ............ Deputy Chairperson;

c) the Chairperson of Tourism Board ... member;

መ) በሰብሳቢው የሚሰየሙ አግባብ ያላቸውን ሚኒስቴሮች የሚመሩ ሚኒስትሮች፣ የክልል ፕሬዚዳንቶች እና የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ከንቲባዎች ....................................አባላት፣

ሠ) የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ........................... አባል፣

ረ) የኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተርስ አሶስየሽን ፕሬ ዚዳንት................................. አባል፣

ሰ) የሆቴሎች እና ሬስቶራንቶች አሰሪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት.......................... አባል፣

ሸ) የሆቴል ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት .............................. አባል፣

ቀ) የቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ......................................... አባል፣

በ) የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ......................................... አባል፣

ተ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተወካይ....................... አባል፣

ቸ) የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ተወካይ............... አባል፣

ኀ) የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ተወካይ ............................ አባል፣

ነ) የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ተወካይ ............... አባል፣

ኘ) የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ተወካይ....................... አባል፣

አ) በሰብሳቢው የሚሰየሙ የግል ባለሀብቶችና ታዋቂ ግለሰቦች.........................አባላት፣

ከ) የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር...............ፀሃፊ፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የፌደራልና የክልል ባለስልጣናት እንዲሁም የኤክስፐርት አስተያየት እንዲያቀርቡ የሚጋበዙ ባለሙያዎች በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፭. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በአሪቱ የሚካሄዱ የቱሪስት መዳረሻዎች ልማት እና የቱሪዝም ማርኬቲንግ ሥራዎች የእድገትና የልማት አቅጣጫዎችን በበላይነት የመምራት፣

፪/ የቱሪዝም ሴክተርን እድገት የሚገቱ ዋና ዋና ማነቆዎችና ቁልፍ ችግሮች እንዲፈቱ አስፈላጊውን መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት የመስጠትና ተፈጻሚነታቸውን የማረጋገጥ፣

d) ministers heading relevant ministries to be designated by the Chairperson, presidents of regions, and mayors of Addis Ababa and Dire Dawa cities ……………….. members;

e) Chief Executive Officer of the Ethiopian Airlines………………………… member;

f) President of Tour Operators Association of Ethiopia ………………….. member;

g) President of Hotel and Restaurants Owners Association of Ethiopia ……….. member;

h) President of Hotel Professional Association of Ethiopia ………………………… member;

i) President of Tourism Professionals Association of Ethiopia……… member;

j) President of the Ethiopian Chamber of Commerce ……………………... member;

k) representative of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church ……………... member;

l) representative of the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council ……..… member;

m) representative of the Ethiopian Catholic Church ………………………… member;

n) representative of the Evangelical Churches Fellowship of Ethiopia ………. member;

o) representative of the Ethiopian Evangelical Church Mekanyesus ………... member;

p) private investors and renowned personalities appointed by the Chairperson ………….. …………………………………… members;

q) Director General of the Organization …… ……………………………………..secretary.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Council may allow other federal and regional authorities and professionals that provide expert opinions to attend its meetings, as required.

5. Powers and Duties of the Council

The Council shall have the powers and duties to:

1/ provide leadership and set directions for the country's tourist destinations development and tourism marketing initiatives;

2/ give the necessary instructions to concerned bodies to remove major impediments and critical challenges to the tourism sector development, and ensure their implementation;

፫/ ለቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ ሥራዎች ስኬታማነት የተለያዩ ተቋማት ድጋፍና ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር አስፈላጊውን መመሪያ የመስጠት፤

፬/ ድርጅቱ ሊከተላቸው በሚገቡ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ የመስጠት፡፡

፮. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

፩/ ምክር ቤቱ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ወይም በምክትል ሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት</u>

፯. <u>መቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፰. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፎችን ሊከፍት ይችላል፡፡

፱. <u>የድርጅቱ ዓላማ</u>

የድርጅቱ ዓላማ በአገሪቱ የተፈጥሮ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም ሌሎች መስህቦች ላይ ተመስርቶና የቱሪዝም ተዋንያንና ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀትና በመምራት የቱሪስት መዳረሻ ልማትና የቱሪዝም ማርኬቲንግ ሥራዎች ዘላቂና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነታቸው እንዲረጋገጥ በማድረግ ከቱሪዝም የሚገኘውን ጠቀሜታ ማጎልበት ይሆናል፡፡

3/ provide the necessary direction to ascertain collaboration and synergy among various institutions for successful implementation of tourism development and marketing initiatives;

4/ set directions on strategic matters that the Organization shall pursue.

6. **<u>Meetings of the Council</u>**

1/ The Council shall meet once every six months; provided, however, that it may meet at any time at the call of the Chairperson or the Deputy Chairperson, as required.

2/ The presence of more than half of the members of the Council shall constitute quorum.

3/ The Council shall pass decisions through majority votes; and in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedures.

## **<u>PART THREE</u>**

## **<u>THE ETHIOPIAN TOURISM ORGANIZATION</u>**

7. **<u>Establishment</u>**

1/ The Ethiopian Tourism Organization (hereinafter the "Organization") is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.

2/ The Organization shall be accountable to the Ministry.

8. **<u>Head Office</u>**

The Organization shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

9. **<u>Objective of the Organization</u>**

The objective of the Organization shall be to enhance benefits of tourism based on potentials of the country's natural, historic, cultural and other attractions in a sustainable and globally competitive manner, and by mobilizing and providing leadership to tourism sector actors and stakeholders towards tourism destinations and marketing development.

፲. **የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር**

ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ የማገልገል፤

፪/ የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች በማቀናጀትና በመምራት የአገሪቱን የቱሪዝም ሃብቶች በውጭ አገርና በአገር ውስጥ የማስተዋወቅ፤

፫/ የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦችና አገልግሎቶች መረጃ ማዕከላትን በመግቢያ በሮችና በማዕከል የማደራጀት፣ የማስተባበርና የመምራት፤

፬/ የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ፤

፭/ የማርኬቲንግ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ መረጃዎችንና የጥናት ዓይነቶችን የመለየት፣ የማሰባሰብ፣ የመተንተን፣ የማደራጀት እና የማሰራጨት፤

፮/ የቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ የአገልግሎት ክፍተት በመለየት የስልጠና ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤

፯/ ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር የመፍጠር፤

፰/ ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የልማት ክፍተት በጥናት በመለየት የሚለሙበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ የማበረታታት፤

፱/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮች የማካሄድ፤

፲/ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፎች በማዘጋጀት ስራ ላይ የማዋል፤

፲፩/ በውጭ አገር ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር ትብብራዊ ግንኙነት የመመሥረት፤

፲፪/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

፲፫/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

፲፩. **የድርጅቱ አቋም**

ድርጅቱ፡-

፩/ የቱሪዝም ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

10. **Powers and Duties of the Organization**

The Organization shall have the powers and duties to:

1/ function as secretariat of the Council;

2/ promote the country's tourism resources domestically and abroad by organizing and coordinating tourism marketing initiatives of the various stakeholders;

3/ set up, coordinate and direct gateways in-country tourism attractions and facilities information centres;

4/ originate and put into effect tourism attraction, product and service brands and update them timely;

5/ identify, collect, analyze, organize and communicate data and study types suitable for conducting marketing operations;

6/ facilitate the addressing of training needs by assessing tourism development and marketing service gap;

7/ establish collaboration and partnership with tourism actors;

8/ identify existing and new tourist destinations development gaps and facilitate their development, and promote the participation of the private sector in the development of same;

9/ conduct studies and research that enable its objectives to attain the desired goals;

10/ formulate and implement frameworks to forge cooperation among regional tourism organs;

11/ establish alliance with overseas similar institutions;

12/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

13/ carry out other related activities necessary for the attainment of its objective.

11. **Structure of the Organization**

The Organization shall have:

1/ a Tourism Board (hereinafter the "Board");

2/ a Director General, and Deputy Director Generals as deemed necessary, to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

**፲፪. የቦርዱ አባላት**

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትና ከግሉ ዘርፍ ተውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

**፲፫. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በምክር ቤቱ በሚሰጡ አጠቃላይ አቅጣጫዎች ላይ በመመስረት የአገሪቱን መልካም ገጽታና ዘላቂ ተወዳዳሪነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ የቱሪስት መዳረሻዎች ልማት እና የቱሪዝም ማርኬቲንግ ሥራዎች በድርጅቱ መከናወናቸውን የመከታተል፤

፪/ በአገሪቱ የቱሪስት መዳረሻ ልማት ስራዎች እንዲጠኑና የቱሪዝም አማራጮች እንዲስፋፋ አቅጣጫ የመስጠት፤

፫/ ለዘላቂ የቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ ስራዎች አስፈላጊ የሆኑ የድጋፍ አግባቦችን እየለየ ለተግባራዊነታቸው ክትትል የማድረግ፤

፬/ የድርጅቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት የመምራት፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀቱ ለሚኒስቴሩ ከመተላለፉ በፊት የመመርመርና የማጽደቅ፣ የሥራ አፈፃፀሙን የመገምገም፤

፭/ የድርጅቱን የሥራ መመሪያዎች የማጽደቅ፤

፮/ እንደአስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን የማቋቋም፡፡

**፲፬. የቦርዱ ስብሰባዎች**

፩/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቦርዱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፭. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ የተመለከቱትን የድርጅቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

**12. Members of the Board**

Members of the Board, including the Chairperson, shall be drawn from the relevant government organs and the private sector, and be appointed by the government. Their number shall be determined as necessary.

**13. Powers and Duties of the Board**

The Board shall have the powers and duties to:

1/ oversee that tourism development and tourism marketing activities are carried out by the Organization to uphold the country's image and sustainable competitiveness;

2/ provide guidance for scrutinizing tourist destination development initiatives and for extending tourism alternatives;

3/ identify suitable ways necessary for backing sustainable tourism development and marketing operations and follow up their realization;

4/ oversee the overall operations of the Organization; review and approve the Organization's work programs and budgets prior to their submission to the Ministry; and evaluate performance of the Organization;

5/ approve the Organizaion's operational directives;

6/ set up various committees as necessary.

**14. Meetings of the Board**

1/ The Board shall meet once a month; provided, however, that it may meet at any time at the call of the Chairperson, as required.

2/ The presence of more than half of the members of the Board shall constitute quorum.

3/ The Board shall pass decisions through majority votes; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of procedures.

**15. Powers and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Organization and shall, subject to general directions of the Board, direct and administer the activities of the Organization.

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Organization specified under Article 10 of this Regulation;

ለ) የድርጅቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የድርጅቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የድርጅቱን ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በቦርዱ ሲጸድቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለድርጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል፤

ረ) የድርጅቱን የሥራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለድርጅቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፲፮. <u>በጀት</u>

የድርጅቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

፲፯. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

፩/ ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የድርጅቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

፲፰. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሃሴ ፳፩ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

b) employ and administer employees engaged in support services of the Organization in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Organization, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and, upon approval by the Board, submit to the Ministry the annual work programs and budgets of the Organization, and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Organization;

e) represent the Organization in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Organization.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Organization to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Organization.

16. <u>Budget</u>

The Organization's budget shall be allocated by the government.

17. <u>Books of Accounts</u>

1/ The Organization shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Organization shall be audited annually by the Auditor General or an Auditor assigned by him.

18. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 27th day of August, 2013

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ